የመረጃ ወረቀት : ፕሮጄስቲን ተከላ (PROGESTIN IMPLANT)

ያስታውሱ፣ የተቀበረው ኢምፕላንት በጾታዊ ግንኙነት ከሚተላለፉ የአባላዘር በሽታዎች ወይም ከኤችአይቪ (HIV) አይከላከልም። እራስዎን ለመጠበቅ በሁሉም ጊዜ ኮንዶም ይጠቀሙ!



## የተቀበረው ኢምፕላንት እንዴት ነው የሚሰራው?

- የሚቀበረው የፕሮጄስቲን ኢምፕላንት የክብሪት እንጨት የሚያክል ቀጭን የፕላስቲክ ቱቦ ነው። የጤና ባለሙያ በላይኛው ክንድዎ ቆዳ ስር ያስገባዋል።
- የተቀበረው ኢምፕላንት ልክ እንደ ሰውነትዎ ሆርሞን ፕሮጄስትሮን ይለቃል። የሚሠራው በማህፀን በርዎ ውስጥ ያለው ፈሳሽ በጣም ወፍራም እንዲሆን በማድረግ የወንድ የዘር ፍሬ እንዳይገባ በማድረግ ነው። የወንድ የዘር ፍሬ ወደ እንቁላሉ መድረስ ካልቻለ ማርገዝ አይችሉም ማለት ነው።
- ኢምፕላንቱ ከተቀበረ እስከ 5 ዓመት ድረስ ይቆያል።
- የቱም ዓይነት የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ 100% ውጤታማ አይደለም። ኢምፕላንቱ ከ99% በላይ ውጤታማ ነው።

## ኢምፕላንቱ እንዴት እጠቀማለሁ?

- ቆዳዎን ማደንዘዣ ከተወጉ በኋላ፣ የጤና ባለሙያ በላይኛው ክንድዎ ቆዳ ስር ኢምፕላንቱን ያስገባዋል። ይህ ጥቂት ደቂቃዎችን ይወስዳል። በቢሮ ወይም ክሊኒክ ውስጥ ይከናወናል።
- ኢምፕላንቱን ከተቀበረ በኋላ ቦታውን ንፁህ እና ደረቅ አድርገው ቢያንስ ለ24 ሰዓታት መጠበቅ አለብዎት።
- በክንድዎ ከተቀበረ በኋላበመጀመሪያዎቹ 7 ቀናት ውስጥ ኮንዶምን እንደ ማስተማመኛ መጠቀም አለቦት።

## የተቀበረው ኢምፕላንት እንዴት ነው ሊጠቅመኝ የሚችለው?

- የተቀበረው ኢምፕላንት አስተማማኝ እና ውጤታማ የወሊድ መከላከያ ነው። አንዴ ከተቀበረ፣ በራሱ ይሰራል - ምንም ነገር ማድረግ የለብዎትም።
- ጡት በማጥባት ጊዜ የሚቀበረውን መጠቀም ይችላሉ።
- ኤስትሮጅንን የያዙ ዘዴዎችን ለማስወገድ ለሚመርጡ ሰዎች ኢምፕላንት መቅበር በጣም ጥሩ አማራጭ ነው።
- አንድ ኢምፕላንት ከተቀበረ ለ5 ዓመታት መጠቀም ይችላሉ። ረዘም ላለ ጊዜ ለመጠቀም ከፈለጉ ከ 5 ዓመታት በኋላ አዲስ ኢምፕላንት ማስቀበር ይችላሉ። ካልወደዱት ወይም ለማርገዝ ከወሰኑ፣ ሐኪምዎ 5 ዓመታት ከመሙላቱ በፊት የተቀበረውን ማስወገድ ይችላል።

## የተቀበረውን ኢምፕላንት ስጠቀም ምን ይሰማኛል?

- የተቀበረው ኢምፕላንት የወር አበባ ለውጥ ያመጣል። ብዙዎች  አልፎ አልፎ ቀላል የወር አበባ መፍሰስ ያጋጥማቸዋል። ይህ ቀላል ደም መፍሰስ ደግሞ የተቀበረው ኢምፕላንት እስኪወገድ ድረስ ሊቀጥል ይችላል። ይህ የተለመደ ነው።
- ጥቂት  ሰዎች ደግሞ የፀባይ ለውጥ፣ የክብደት መጨመር፣ ብጉር እና/ወይም በላይኛው ክንድ ላይ የቆዳ ቀለም ለውጥ ያሳያሉ።
- የተቀበረው ኢምፕላንት ሲወገድ አብዛኛዎቹ የጎንዮሽ ጉዳቶች ይጠፋሉ።

## ሰዎች በክንዴ ላይ የተቀበረው ኢምፕላንት ማየት ይችላሉ?

- አብዛኛዎቹ ኢምፕላንቶች ሊታዩ አይችሉም፣ ነገር ግን የተቀበረው ኢምፕላንት ላይ ያለውን ቦታ ከነኩት ሊሰማዎት ይችላል።

## የተቀበረው ኢምፕላንት አደጋዎች አሉት?

- የተቀበረው ኢምፕላንት በጣም አስተማማኝ ነው።
- ኢምፕላንቱ ከተቀበረ በመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ ከሚከተሉት ምልክቶች አንዱ ካለዎት ሐኪምዎን ያናግሩ:-
  - በክንድዎ ላይ መቅላት፣ ሙቀት፣ ወይም ፈሳሽ ነገር ሲኖር።
  - ትኩሳት (>101°ፋ)
- የተቀበረው ኢምፕላንት በሚጠቀሙበት በማንኛውም ጊዜ የሚከተሉት ምልክቶች ካሉዎት የህክምና ባለሙያዎን ያናግሩ፡
  - የእርግዝና ስሜት (የጡት ህመም፣ ማቅለሽለሽ)
  - በቤት ውስጥ የእርግዝና ምርመራ አዎንታዊ  ሆኖ ከመጣ

This publication is supported by the Office of Population Affairs (OPA) of the U.S. Department of Health and Human Services (HHS) as part of a financial assistance award totaling $1,361,220. The contents are those of the author(s) and do not necessarily represent the official views of, nor an endorsement, by OPA/OASH/HHS, or the U.S. Government.